# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

## የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ፣ ቅጥያ፣ ጥገና እና ኦኘሬሽን ሥራዎች አፈፃፀም
## መመሪያ ቁጥር 16/2012

# መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ያለው የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓት በተቀናጀ መንገድ ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጠ ባለመሆኑ፤

የከተማውን የእድገት ደረጃ በሚመጥን መልኩ የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓትን ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ እና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በቀጣይነትም ሰፊ እቅድ ተይዞ እየተሰራ በመሆኑ፤

ፍሳሽ በዘመናዊ መልኩ የማስወገድ ሽፋንን ለማሳደግ የሚያስችሉ በዘርፉ ተጨማሪ የማጣሪያ ጣቢያ ማስፋፊያ እና የፍሳሽ መስመር ግንባታ ፕሮጀክቶች ግንባታዎች በቅርቡ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የሚጀምሩ በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ባለው መመሪያ ላይ ተመስርቶ ከተቋቋመው አሰራር በተሻለ በመስሪያ ቤቱ አነሳሽነትም ሆነ በደንበኞች ጥያቄ መሠረት የፍሳሽ መስመር ለደንበኞች ስለሚቀጠልበት መንገድ መወሰን በማስፈለጉ፤

የባለስልጣን መ/ቤቱን የደንበኞች ተግባር እና ሃላፊነት በግልፅ ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በባለስልጣን መ/ቤቱ የፍሳሽ መስመር ዝርጋታን፣ የደንበኞች ቅጥያ፣ ጥገና እና የኦፕሬሽን ሥራዎችን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ ተጠያቂነትንና እና ግልጽ የሆነ አሰራር ለማስፈንና ወጥ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት በመታመኑ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>አንቀጽ /1/</u>

## <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ውሃና ፍሰሽ ባለስልጣን የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ፣ ቅጥያ፣ ጥገና እና ኦፕሬሽን ሥራዎች አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 16/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ /2/</u>

## <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የሚከተሉት ቃላትና ሀረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡

1. **"ባለስልጣን"** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ማለት ነው፤
2. **"ዋና ሥራ አስኪያጅ"** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
3. **"ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ"** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
4. **"ሥራ አስኪያጅ"** ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የቅ/ጽ/ቤቶች ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
5. **"ዘርፍ"** ማለት ፡- የፍሳሽ ቆሻሻ ማንሳትና ማስፋፋት አገልግሎት ም/ዋ/ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፤
6. **"ንዑስ የሥራ ሂደት"** ማለት፡- በዋናው መ/ቤትና በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኙ የፍሳሽ ዘርፍ ንዑስ የሥራ ሂደት ማለት ነው፤
7. **"ሠራተኛ"** ማለት፡- በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ለተወሰነ ጊዜና ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ማለት ነው፤
8. **"ፍሳሽ"** ማለት፡-የተጣራ ውሃ ለመኖሪያ ቤት፤ለንግድ፤ለኢንዱስትሪ፤ ወይም ለማኅበራዊ አገልግሎት ከዋለ በኃላ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባስቀመጠው የጥራት ደረጃ የተበከለ ውሃ ሲሆን ይኽም የመፀዳጃ ቤት ቆሻሻ እጣቢ እና የእነኚሁኑ ዝቃጮች ይጨምራል፤
9. **"የፍሳሽ መስመር"** ማለት፡-የተያያዙ የፍሳሽ ማስወገጃ መሥመሮችን እንዲሁም በፍሳሽ መሥመሩ ላይ የሚኖሩት ማንሆሎች፤ የወንዝ መሻገሪያዎች እና የደንበኛ መስመር ጭምር ነው፤
10. **"የሕዝብ ፍሳሽ መሰመር"** ማለት፡- ባለስልጣኑ ለፍሳሽ ማስወገጃ አገልግሎት እንዲውል የተዘረጋው የመንግስት የፍሰሽ መስመር ማለት ነው፤

11. **“ደንበኛ ”**ማለት፡- ፍሳሽ በመሰመር ለማስወገድ ከባለስልጣኑ የሕዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር በሕጋዊ መንገድ ያገናኘ ማለት ነው፤
12. **“ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ”** ማለት፡- ማዕከላዊ የፍሳሽ መረብ ባልተዳረሰባቸው አከባቢዎች በሙሉ ወይም በከፊል ፍሳሽን አጣርቶ የሚያሰውግድ ማጣርያ ማለት ነው፤
13. **“ጀት ማስተር”** ማለት፡- የተዘጋ የፍሳሽ መስመር ለመክፈት የሚያገለግል ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡
14. **“ከፍተኛ የፍሳሽ መስመር”** ማለት፡- 500 ሚሊ ሜትር ዲያሜትር እና ከዛ በላይ ስፋት ያለው የተዘረጋ ፍሳሽ መስመር ማለት ነው፡፡
15. **“መለስተኛ የፍሳሽ መስመር”** ማለት፡- 400 ሚሊ ሜትር ዲያሜትር እና ከዛ በታች ስፋት ያለው የተዘረጋ ፍሳሽ መስመር ማለት ነው፡፡
16. **“ቅጥያ”** ማለት፡- ከደንበኛው ቤት እስከ የሕዝብ የፍሳሽ መስመር የሚገናኝበት ቦታ ማለት ነው፡፡
17. **“ሴክሽን ትራክ”** ማለት፡- የተጠራቀመ ፍሳሽ ለማንሳት የሚያገለግል ተሽከርካሪ ማለት ነው
18. **"ሶስተኛ ወገን"** ማለት፡- ከባለስልጣኑ ጋር የፍሳሽ ማስወገድ አገልግሎት የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ፤ ቅጥያ፤ውል የሌለው አካል ማለት ነው፡፡
19. " **የጋራ መኖሪያ ቤት"** ማለት፡- በአዲስ አበባ ከተማ በቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት በኩል የሚገነቡ እና እድለኛ ለሆኑ ነዋሪዎች በዕጣ የተላለፉ ወይም የሚተላለፉ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የተከራዩ ወይም የሚከራዩ ቤቶች ማለት ነው፡፡
20. **"ሪልስቴት"** ማለት ፡-በከተማው ክልል ውስጥ የግል ድርጅቶች መሬት በሊዝ በመግዛት የሚገነቧቸው እና ለግለሰቦች መኖሪያነት በሽያጭ የሚያስተላለፏቸው የግል መኖሪያ ቤቶች ማለት ነው፡፡
21. **"የመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋም"** ማለት ፡- በአዲስ አበባ ከተማው አስተዳደር የተቋቋሙ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን እንደ መንገድ ፤ውሃ ፤ስልክ ፤መብራት ፤ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ፤ ተቋማት ማለት ነው፡፡
22. " **የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ"** ማለት፡- በአዋጅ ቁጥር 47/1967 ዓ.ም በመንግስት የተወረሱ የከተማ ትርፍ ቤቶችን የማስተዳደር እና ገንብቶ የማከራየት ጭምር ስልጣን የተሰጠው ተቋም ነው፡፡
23. ደረጃ **"ሀ፣ለ፣ሐ"** ማለት፡- በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 የተቀመጠ የግብር ከፋይ ደረጃዎች ናቸው፡፡
24. "ሳድል" ማለት የደንበኛ ፍሳሽ መስመር ቅጥያ የሚውል መገጣጠሚያ ነው፡፡

25. "ማንሆል" ማለት በፍሳሽ መስመር ዝርጋታ አቅጣጫ መቀየር ሳያስፈልግ ፣ ርዝመት ከተወሰነ ሜትር በላይ ሲሆን ፣ ከፍታ ልዩነት ሲሰፋ የሚገነባ የፍሳሽ መስመር አካል ነው፡፡

26. "ኮንዶሚኒያል አይነት" ማለት የደንበኛ ፍሳሽ መስመር ቅጥያ ለአንድ አካባቢ በጋራ የሚሰጥበት መንገድ ነው፡፡

## አንቀጽ /3/

## የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የሥራ መሪዎች እና ሠራተኞች፣ የመስመር ዝርጋታ ፣ቅጥያና ጥገና ኦፕሬሽን ሥራዎች በሚሰሩ የስራ ተቋራጭ ወይም ማህበር እንዲሁም አገልግሎቱን በሚፈልጉ ደንበኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ /4/

## የፍሳሽ መስመር ዝርጋታና አገልግሎት አሰጣጥ

4.1. የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ከከተማው ማስተር ኘላንና ከፍሳሽ ማስተር ፕላን ጋር የተናበበና የተጣጠመ መሆን ይኖርበታል፤

4.2. የህዝብ የፍሳሽ መስመር ከ ባለንብረቱ ድንበር እስከ 6 ሜትር ድረስ መዘርጋትና መጠገን በባለስልጣኑ አማካኝነትና ወጭ የሚደረግ ይሆናል፡፡

4.3. ከግቢው ውስጥ ያለውን የተበከለ ውሃ መገልገያ መስራት ወይም ማሻሻል እና መገልገያውን ከህዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር እስከሚገናኝበት ድረስ መዘርጋት ወይም ማሻሻል በባለንብረቱ ወጭ የሚሰራ ሆኖ ባለስልጣኑ ከጥራትና ተገቢ ዋጋ አንፃር እንደአስፈላጊነቱ በራስ ኃይል ወይም ከባለስልጣኑ ጋር በሚዋዋሉና በውሃና ፍሳሽ ዘርፍ በሰለጠኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ያሰራል፡፡

4.4. ከባለንብረቱ ድንበር 3 ሜትር ርቀት የህዝብ የፍሳሽ መስመር ተዘርግቶ ከሆነ ባለንብረቱ የግል የፍሳሽ መገልገያውን እንዲዘረጋና ከህዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር እንዲያገናኝ ባለስልጣኑ ሊያስገድደው ይችላል፡፡

4.5. የሕዝብ የፍሳሽ መስመር እስከ ደንበኛው ድንበር 6 ሜትር ርቀት ቀርቦ ካልተገኘ ደንበኛው የግል የፍሳሽ መስመር ቅጥያ ቢጠይቅ የሕዝብ መስመሩ የመቀበል አቅም ካለው ደንበኛው ለዲዛይንና ለግንባታ የሚያስፈልገውን ወጪ ሸፍኖ መስመሩ ሊዘረጋለት ይችላል፤

4.6. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 4.1 መሠረት ደንበኛው የዘረጋው መስመር የሌላ ደንበኛን ፍሳሽ ለመቀበል የሚችል ሆኖ ሲገኝና ባለስልጣኑ ሲያዝ ቅጥያውን ማካሄድ ይችላል፡፡ ለባለመስመሩ የወጣውን ወጪ የድርሻውን በማስላት ተገቢውን ካሳ በሚያስቀጥለው ደንበኛ እንዲከፈለው ባለስልጣኑ ያደርጋል፡፡ ደንበኛው የባለሥልጣኑን ውሳኔ በመቃወም የመስመር ቅጥያ ተግባሩን ሊያውክ አይችልም፡፡

4.7. ከፍተኛ ፍሳሽ መስመር ዝርጋታ በዋናው መ/ቤት ስር በሚገኙ ንዑስ ሥራ ሂደቶችና እንደአስፈላጊነቱ በፕሮጀክት ፅ/ቤቶች ህጎችን ጠብቆ ይዘረጋል፡፡

4.8.የመለስተኛ ፍሳሽ መስመር ዝርጋታ በቅርንጫፍ ጽ/ቤትና እንዳስፈላጊነቱ በዋናው መ/ቤት፤ በኘሮጀክት ጽ/ቤት ህጎች ጠብቆ ይዘረጋል፤ ክትትል ያደርጋል፣

4.9.የፍሳሽ መስመር ለመዘርጋት የሚቆፈረው ጉድጓድ ከ2 ቀን በላይ ክፍት ሆኖ መቆየት የለበትም፤

4.10.የፍሳሽ መስመር ለመዘርጋት ተቆፍሮ ከተመለሰው የተረፈ አፈር በ3 ቀን ውስጥ መነሳት አለበት፤

4.11.በቁፋሮ ስራ ላይ ስለመሆኑ በአካባቢው የማስጠንቀቂያ ምልክት መደረግ እና የመከላከያ ዘዴውንም ማበጀት አለበት፤ በዚህ ሳብያ ለሚፈጠር አደጋ ሥራውን የሚያሰራው አካል ተጠያቂ ይሆናል፤

4.12.የተመለሰው አፈር ደረጃውን ጠብቆ በ 10 ቀንት ውስጥ መጠቅጠቅ አለበት፤

4.13.በፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ሥራ የሚደርስ ጉዳት በአፋጣኝ ለሚመለከተው አካል መቅረብ አለበት ፣ ደንበኛው ለቅርንጫፍ ፣ ቅርንጫፉ ለዘርፉ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

## <u>አንቀፅ /5/</u>

## <u>የፍሳሽ መሥመር ቅጥያ አገልግሎት አሰጣጥ</u>

1. ባለስልጣኑ የደንበኛው የግል ፍሳሽ መስመር ከሕዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር እንዲገናኝ የሚያደርገው የህዝብ የፍሳሹ መስመር ከደንበኛው ይዞታ ወይም ንብረት አካባቢ የተዘረጋ መሆኑን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፤
2. ባለስልጣኑ የሚቀርብለትን የፍሳሽ መስመር ቅጥያ የሚያከናውነው ከሌሎች መ/ቤቶች የሚጠየቅ ፈቃድ ካለ (የመንገድ ማሰበሪያ እና የመሳሰሉትን) ደንበኛው በራሱ በሟሟላት እንዲፈፀም ያደርጋል፣
3. የግል የፍሳሽ መስመር ቅጥያ የሚደረግለት መኖሪያ ቤት/ድርጅት በውሃ የሚሰራ መፀዳጀ ቤት (Flash toilet) ያለው ሆኖ የሚወገደውን ፍሳሽ የለየና የራሱ የውስጥ መስመር ሲኖረው ነው፤

4. የደንበኞች ቅጥያ የሚፈፀመው በሳድል፣ በኮንዲሚኒየም አይነት(ለአንድ አካባቢ በጋራ) ወይም በማንሆሎ የቅጥያ አይነት ሊሆን ይችላል፣

5. የግል የፍሳሽ መስመር ከሕዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር ለማገናኘት በቴክኒክ ረገድ የሚቻል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ነገር ግን በመሬት ስበት ኃይል አገልግሎት መስጠት ካልተቻለና በደንበኛው ወጪ የፍሳሽ መግፊያ ፓምኘ በመጠቀም የፍሳሽ መስመሩ ተጠቃሚ ለመሆን የጠየቀ እንደሆነ የውል ግዴታ በመግባት ለደንበኛው አገልግሎት ሊሰጠው ይችላል፤

6. ከደንበኛው ግቢ ውስጥ የሚወጣው ፍሳሽ ወደ የሕዝብ የፍሳሽ መስመር ከመያያዙ በፊት ቅድመ ማጣሪያ አገልግሎት መገንባት አስፈላጊ ሲሆን ደንበኛው በባለስልጣኑ መመሪያ እና ዲዛይን መሠረት ማጣሪያውን በአግባቡ መገንባቱንና ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ባለስልጣኑ ሲያረጋግጥ የደንበኛው የፍሳሽ መስመር ከሕዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር እንዲገናኝ ይደረጋል፤

7. ደንበኛው በንዑስ አንቀፅ 5.2፣ ንዑስ አንቀፅ 5. 2.6. መሠረት የቅደመ ማጣሪያ ግንባታ አጠናቅቆ ሥራ ላይ ካዋለ በኂላ የታቀደውን የአሰራር ሂደትና ጥራት ደረጃ ጠብቆ የሚሰራ መሆኑንና እንዲሁም ከማጣሪያው የሚወጣ የፍሳሽ ይዘትና የጥራት ደረጃ የባለስልጣኑን ደረጃ የሚያሟላ ስለመሆኑ ባለስልጣኑ በየወቅቱ ክትትል ያደረጋል፤

8. የቅድመ ማጣሪያው አሰራርና ከማጣሪያው የሚወጣው የፍሳሽ ጥራት ደረጃውን የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ ለደንበኛው እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አስራ አምስት ቀን የሚደርሰ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የግል ቅጥያውን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡ በዚህ ሂደት ፍሳሽ ስርዓቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ደንበኛው ኃላፊ ይሆናል፤

9. የፍሳሽ መስመር ለመዘርጋት/ለመጠገን ወደ ቁፋሮ ከመግባቱ በፊት ከመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት ጋር አስፈላጊው ፍቃድ ሊኖር ይገባል፤

10. ለደንበኞች ቅጥያ ሲፈፀም የሚጠይቅ ፍቃድ ካለ ደንበኛው ከሚመለከታቸው ተቋማት ፌቃድ እንዲጨርሰ ይደረጋል፡፡

11. በፍሳሽ መሠመር ቅጥያ ስራ የሚደርስ ጉዳት በአፋጣኝ ለሚመለከተው አካል መቅረብ አለበት፤ ደንበኛው ለቅርንጫፍ፣ ቅርንጫፍ ለዘርፍ የማሳወቅ ሃላፊት አለበት፡፡

12. ለአንድ ደንበኛ ይዞታ አንድ የፍሳሽ መስመር ቅጥያ ብቻ ይደረግለታል፡፡ ነገር ግን የቦታው አቀማመጥ የማይፈቅድ ከሆነ በቅርንጫፍ ን/ሥ/ሂደቱ ውሳኔ ተጨማሪ ቅጥያ ሊደረግ ይችላል፤ ይህ በሚሆንበት ወቅት ለተጨማሪ ቅጥያ ደንበኛው አስፈላጊውን ክፍያ አስቀድሞ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

13. ለመንግስት የጋራ መኖሪያ ቤቶች የሕንፃ ዙርያ ፍሳሽ መስመር፤ የዋና ፍሳሽ መስመር፤ ያልተማከለ የፍሳሽ ማጣርያ ግንባታ እና የቅጥያ ሥራውን ወጪ አሰሪው አካል እንዲሸፍን ሆኖ ግንባታው በባለስልጣኑ ይፈፀማል፡፡

14. የሪል ስቴት አልሚዎች የህንፃ ዙሪያ የፍሳሽ መስመር ዝርጋታን ደረጃውን በጠበቀ ስታንዳርድ መሰረት መሰራቱን የባለስልጣኑ ባለሙያዎች ሲረጋገጥና በአካባቢው የተዘጋ የሕዝብ ፍሳሽ መሰመር ፍሳሽን የመቀበል አቅም ካለው የቅጥያውን ወጪ ሸፍኖ ሊቀጠልለት ይችላል፤
15. ከላይ በአንቀጽ 6.13 ለተጠቀሰው የፍሳሽ መስመር ከሌለ በራሱ የፍሳሽ ማጣሪያ በመገንባት ፍሳሽ አጣርቶ የማስወገድ ግዴታ አለበት፣
16. የባለስልጣኑ ባለሙያዎች እንደ የሁኔታው የግል ይዞታ ግቢ ውስጥ በማንኛውም ሰዓት ገብተው ህገወጥ ቅጥያ መኖሩንና ያልተፈቀዱ ነገሮች ወደ ፍሳሽ መስመር መለቀቃቸውን የመቆጣጠርና የማስተካከያ ትዕዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ሰራተኞቹ ይህንን ድርጊት ሲያከናውኑ የበላይዞታው ሰላምና ፀጥታ በማያውክ ሁኔታና ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ በማሳየት ይሆናል፤
17. የከፍተኛም ሆነ የመለስተኛ የፍሳሽ መስመር በዓመት ቢያንስ ለአራት ጊዜ ፍተሻ መደረግ አለበት፤
18. በዋ/መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤት ለሚከናወኑ የፍሳሽ መስመር ዝርጋት ፤ቅጥያ፣ ጥገናና ኦፐሬሽን ስራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማካሄድ እንዲያስችል ቢያንስ ለአንድ ወር የሚያስፈልገውን ዕቃ ከግምጃ ቤት በማውጣት በራሱ መለስተኛ ግምጃ ቤት ይይዛል፡፡
19. የፍሳሽ መስመር ዝርጋት፣ ቅጥያ፣ ጥገናና ሥራው ሲጠናቀቅ ለስራው የወጣው ዕቃ፣ የሰው ኃይል የማሽነሪ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የያዘ የማጠናቀቂያ ሪፖርት ስራው በተጠናቀቀ በሶስት ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ክፍያ ከመፈከፈሉ በፊት ማቅረብ አለበት፤
20. ከላይ በአንቀፅ 5.2 ንዑስ አንቀፅ 5.2.19. መሰረት የተረፈ ንብረት ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ መደረግ አለበት፤
21. የአካባቢ የመሬት አቀማመጥ አመቺ ሆኖ ሲገኝ በአንድ ብሎክ ውስጥ የሚገኙ ደንበኞች በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ቅጥያ ሊፈጸም ይችላል፡፡
22. የግል የፍሳሽ መስመር ከሕዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር ለማገናኘት የግንባታው ስራ በባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ የአቅም ውስንነት ካጋጠመው በሶስተኛ ወገን ሊያሰራ ይችላል፤
23. ደንበኛው ግንባታውን በግል የሥራ ተቋራጭ ለማሰራት ሲፈልግ ባለስልጣኑ ዲዛይኑን በማዘጋጀት የግንባታውን ሥራ ተቆጣጥሮ ይሰራል ወይም ያሰራል፡፡ ለዲዛይንና ቁጥጥር ሥራ የሚያስፈልገውን ወጭ ደንበኛው ለባለሰልጣኑ ይከፍላል፡፡
24. ደንበኛው የፍሳሽ መስመር የተቀጠለለትን ህንፃ ለማሻሻል ወይም ተጨማሪ ህንፃ ለመገንባት ሲፈልግ የፍሳሽ መገልገያ ማሻሻያ ለውጥ ከማድረጉ በፊት ከባለሰልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤
25. ነባር የጋራ መኖሪያ ቤቶች፤ የኪራያ ቤቶች፤ የመንግስት ህንጻዎች ወዘተ የፍሳሽ ቅጥያ ሲጠይቁ ክፍያውን ሸፍነው ሊቀጠልላቸው ይችላል፤

## <u>አንቀጽ /6/</u>

## <u>የፍሳሽ መስመር ቅጥያ አገልግሎት ለማገኘት ስለሚቀርብ ጥያቄ</u>

6.1. ደንበኛው የግል የፍሳሽ መስመር ከህዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር እንዲገናኝለት ሲፈልግ ጥያቄውን በፅሁፍ ወይም በኢ-ሜይል ለቅርንጫፍ መ/ቤቱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6.2. የመስመር ቅጥያ ጠያቂው የቤቱ ባለቤት ወይም ሕጋዊ ወኪል መሆኑን የሚያረጋገጥ ሰነድና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ፤ ፓስፖርት፣ ቅጥያ የተጠየቀለት ቤት የውሃ አገልግሎት ያለው ለመሆኑ ለመጨረሻ ጊዜ የውሃ ሂሳብ የተከፈለበትን ደረሰኝ በማቅረብ ውል መዋዋልና ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## <u>አንቀጽ /7/</u>
## <u>ስለፍሳሽ አገልግሎት ክፍያ</u>

7.1. ደንበኛው የፍሳሽ በመስመር ማስወገድ አገልግሎት ክፍያ በወጣው ታሪፍ መሰረት በየወሩ ከውሃ ሂሳብ ጋር እንዲከፍል ይደረጋል፤

7.2. ከአንድ በላይ የውሃ ቆጣሪ ውል ካለው የፍሳሽ በመስመር አገልግሎት ሂሳባ ባለው ቆጣሪ ብዛት ልክ በየወሩ ከውሃ ሂሳብ ጋር የፍሳሽ በመስመር አገልግሎት እንዲከፍል ይደረጋል፤ ደንበኛው ያለውን የውሃ ውል ብዛት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

7.3. የራሳቸው ጉድጓድ ውሃ ያላቸው ደንበኞች እና ለፍሳሽ መስመር ለሚጠቀሙ ደንበኞች የአገልግሎት ክፍያ ባለስልጣኑ ይወስናል፣

7.4. የደንበኛን የፍሳሽ መስመር ከሕዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር ለማገናኛት የሚኖረው የአከፋፈል ሁኔታ

1. በደረጃ ሀ እና ለ የተጠቀሱት የንግድ ድርጅቶች ፤ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም አለም አቀፍ ተቋማት የተጠየቀውን ግምት ሂሳብ በቅድሚያ ሙሉውን ይከፍላሉ ፤

2. ለመኖርያ ቤት አገልግሎት እና ለደረጃ ሐ የንግድ ድርጅቶች

ሀ/ የሕዝብ የፍሳሽ መስመሩ በአቅራቢያው ከ3 እስከ 6ሜትር ከቀረበ ክፍያው ሙሉውን ወይም ከሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ይገደዳል፤

ለ/ የሕዝብ የፍሳሽ መስመሩ በአቅራቢያው ከ6 እስከ 12 ሜትር ከቀረበ ክፍያው ሙሉውን ወይም ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ይደረጋል፤

ሐ/ የአገልግሎት ክፍያ ለመክፈል የሚገደደው የፍሳሽ መስመሩ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር ነው፡፡

7.5 ደንበኛው ውል ከመፈረሙ በፊት ስለውሉ በጠቅላላውና በተለይም ስለአከፋፈል ሁኔታ የተቀመጡትን ግዴታዎች በግልፅ እንዲያውቅና የክፍያ ጊዜውን እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡

7.6. በረዥም ጊዜ መክፈል ከመረጠ ደንበኛው የተፈቀደለትን የተከፋፈለ የአገልግሎት ክፍያ ከውሃ ቢል ጋር ወይም የውሉን ዋና ሰነድ በማያዝ በአካል ቀርቦ እንዲከፍል የሚደረግ ሆኖ የከፈሉበት ደረሰኝ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

7.7. ለመክፈል በተስማሙበት ጊዜ ገደብ ውስጥ ያልከፈለ ደንበኛ ወቅቱን ጠብቆ ላልከፈለበት ጊዜ ደንበኛው በባንክ ወለድ መሠረት የዘገይበትን ጊዜ ቅጣት እንዲከፈል ይደረጋል፡፡ አንድ ወር ከቆየ መስመሩ ተቋርጦ በህግ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

7.8. የቅርንጫፍ ሂሳብ ክፍል ደንበኛው የቅጥያ የአገልግሎት ክፍያው ከውሃ ቢል ጋር ወይም በአካል እንዲቀርብለት የፈረመበትን ውል መሠረት በማድረግ ያለማቋረጥ የሚፈለግበትን ሂሳብ ክፍሎ ማጠናቀቁን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

7.9. የቅርንጫፍ ለደንበኛው የፍሳሽ አገልግሎት ቅጥያ ከተፈፀመ በኃላ መረጃን በማደራጀት በመረጃ ቋት ይያዛል፤

7.10. የተጠናከረውን የደንበኛ መረጃ ለቢል ዥግጅት ማስተላለፊያ ሰነዶችን በመሙላትና በንዑስ የሥራ ሂደቱ እየተረጋገጠ ወርሃዊ የክፍያ ቢል ከውሃ ክፍያ ጋር ቢል እነዲወጣለት ይደረጋል ለዘርፍ ሪፖርት ያቀርባል፤

7.11. የጋራ መኖርያ ቤት/ሪል እስቴት ነዋሪ ደንበኞችን በተመለከተ፤ የውሃ ቅጥያ ውል ሲዋዋሉ የፍሳሽ መሰመራቸው ወደ ተማከለ ወይም ወደ አልተማከለ የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ የሚላክ መሆኑን አረጋግጦ የፍሳሽ አገልግሎት ውል በመዋዋል አገልግሎት ክፍያው ከውሃ ክፍያ ጋር ቢል እንዲወጣለት ይደረጋል፤

7.12. በዚህ አንቀጽ ተ.ቁ. 11. የተመለከተው እንዳለ ሆኖ ቀደም ሲል የፍሳሽ አገልግሎት አያገኙ ያሉ ደንበኞች ሁሉ አዲስ ውል እንዲዋዋሉ ይደረጋል፣

7.13. ደንበኛው በሚፈርመው ውል መሠረት ጊዜውን ጠብቆ የፍሳሽ አገልግሎት ለ1 ወር ክፍያ ካልከፈለ የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት የፍሳሽ መስመር ቅጥያውን በማቋረጥ ለዚህ የወጣውን ወጭ ባለስልጣኑ ይጠይቃል፡፡

7.14. የተቋረጠን የፍሳሽ መስመር መልሶ ለማስቀጠል የሚፈለግበት ክፍያ በመፈፀምና የማስቀጠያ ክፍያ ደንበኛው ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ይቀጠልላታል፡፡

7.15. በአከባቢ የኘላን ወይም በመልሶ መገንባት ለውጥ ምንክያት ለሚከሰት የመስመር ማቋረጥና መልሶ ቅጠላ ደንበኛው ወይም አሰሪው ክፍል ወጪውን የመሸፈን ኃላፊነት አለበት፡፡

## <u>አንቀጽ /8/</u>

## <u>የፍሳሽ መስመር ደህንነት እና ክትትል በተመለከተ</u>

8.1. በባለስልጣኑ የፍሳሽ መስመር ላይ፣ በደንበኛው ግቢ ውስጥ ያሉ መስመሮች ላይ ማንኛውም ነገር እንዳይከማች፤ መስመሮች እንዳይጎዱ፤ እንዳይደፈን፤ እንዳይሰበሩ ደንበኛው ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡

8.2. በዋና መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች የፍሳሽ መስመሮችን ደህንነት የሚከታተል አካል እንዲኖር ይደረጋል፡፡

8.3. የፍሳሽ ማንሆሎች ሳይፈኖች የማፅጃ ኘሮግራም በማዘጋጀት ጊዜው ጠብቆ ክትትል እየተደረገ የማፅዳት ሥራ መስራት ይገባዋል፤

8.4. የፍሳሽ መስመሮች ገንፍለው አከባቢን ከመበከላቸው በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ ሲከስትም በአፋጣኝ እና በተቀመጠው እስታንዳርድ እርምጃ ይወስዳል፡፡

8.5. የፍሳሽ መዳረሻ መንገድ ደጋፊ ግንብ፣ የፍሳሽ መስመር የወንዝ መሸጋገሪያ ድልድዮች ክትትል ይደረጋል፣

8.6. በሶስተኛ ወገን በሚደርስ የፍሳሽ መስመር መሰበር ምክንያት ለሚኖር ጥገና ወጪ በጉዳት አድራጊው በመሃንዲስ ግምት እንዲሸፍን ይደረጋል፤ በተጨማሪም በአካባቢ ላይ ለፈጠረው ብክለት በሚቀርብ ግምት መሰረት ካሳ እንዲከፍል የደረጋል

## አንቀጽ /9/

## የፍሳሽ መስመር ጥገና

9.1. የከፍተኛ ፍሳሽ መስመር ጥገና በዋናው መ/ቤት ደረጃ ህጎች ጠብቆ ይጠግናል፤

9.2. የመለስተኛና ዝቅተኛ ፍሳሽ መስመር ጥገና በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ እና እንደ አስፈላጊነቱ በዋ/መ/ቤት ህጎች ጠብቆ ይጠግናል፤

9.3. የፍሳሽ መስመር ለመጠገን የሚቆፈረው ጉድጓድ ከ2 ቀን በላይ ክፍት ሆኖ መቆየት የለበትም፤

9.4. የፍሳሽ መስመር ለመጠገን ተቆፍሮ ከተመለሰው የተረፈ አፈር በ3 ቀን ውስጥ መነሳት አለበት፤

9.5. በቁፋሮ ስራ ላይ ስለመሆኑ በአካባቢው የማስጠንቀቂያ ምልክት መደረግ እና የመከላከያ ዘዴውንም ማበጀት አለበት፤ በዚህ ሳብያ ለሚፈጠር አደጋ ሥራውን የሚያሰራው አካል ተጠያቂ ይሆናል፤

9.6. የተመለሰው አፈር ደረጃውን ጠብቆ በ 10 ቀናት ውስጥ መጠቅጠቅ አለበት፡፡

9.7. የጋራ መኖሪያ ቤቶች የጥገና ሥራ ከኮኔክሽን ቦክስ ጀምሮ ያለው በባለስልጣኑ ይጠገናል፣

## አንቀጽ 10

## ክልከላ

10.1. ደንበኛው ከህዝብ የፍሳሽ መስመር ግራና ቀኝ እስከ 6 ሜትር ርቀት ባለው ቦታ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታ ወይም ቋሚ ሥራ ማከናወን መስራት ወይም ዛፍ መትከል አይኖርበትም፡፡ ለዚህም አስፈላጊው ክትትል በተቋሙ በየደረጃው ይከናወናል፡፡

10.2. ማንኛውም የፍሳሽ መስመር ደንበኛ ባለስልጣኑ ካልፈቀደ ወይም ከባለስልጣኑ እውቅና ውጭ ወይም ባለስልጣኑ ለደንበኛው ወደ ህዝብ የፍሳሽ መስመር ላይ የራሱን የፍሳሽ መስመር ማገናኘት ወይም ለሌላ ባለንብረት ወደግል የፍሳሽ መስመር እንዲቀጥል መፍቀድ አይቻልም፡፡

10.3. ከባለስልጣኑ ፈቃድ፣ እውቅናና ትዕዛዝ ውጭ ደንበኛው ወደ ህዝብ የፍሳሽ መስመር ቅጥያ ፈጽሞ ቢገኝ ባለስልጣኑ የፍሳሽ እና የውሃ መስመር ቅጥያውን አቋርጦ የደረሰበትን ጉዳት ማለትም ለቅጥያ የሚያስፈልገውን ወጪ እንዲሁም ፍሳሽ ከተቀጠለበት ጊዜ ጀምሮ ለፍሳሽ በመስመር ማስወገጃ ታሪፍ መሰረት ክፍያውን እንዲፈፅም ይደረጋል፤ ባለስልጣኑ

እርምጃ ከመውሰዱ አስቀድሞ የተጠቀሱት ድርጊት መፈፃማቸውን በተገቢ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡

10.4. ደንበኛው የዝናብ ውሃ እንዲሁም ጠጣር ነገር ወደ ሕዝብ የፍሳሽ መስመር ማስገባት አይቻልም፤

10.5. የፍሳሽ ቅጥያ አገልግሎት ቀጥታ ውስጥ ለውስጥ ከተዘረጋ የውስጥ የፍሳሽ መሰመር ላይ ብቻ ይከናወናል፡፡ ከመፀዳጃ ቤት ጉድጓድ /ሲኘቲክ ታንክ መቀጠል አይቻልም፡፡

10.6. በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ቁሶችን ወደ ፍሳሽ መስመር ያስገባ ደንበኛ የውሃና ፍሳሽ መስመሩ በመ/ቤቱ ተቋርጦ ደንበኛውን በህግ እንዲጠየቅ ለህግ አገልግሎት ያስተላልፋል፡፡

10.7. ደንበኛው ያስዘረጋው የፍሳሽ መስመር የሌላ ደንበኛን ፍሳሽ ለመቀበል የሚችል ሆኖ ሲገኝና ባለስልጣኑ ሲፈቅድ ቅጥያውን ማካሄድ የሚቻል ሲሆን ለባለስመስሩ ተገቢውን ካሳ እንዲከፈለው ያደረጋል፡፡ ደንበኛው የባለሥልጣኑን ውሳኔ በመቃወም የመስመር ቅጥያ ተግባሩን ሊያውክ አይችልም፡፡

10.8. ደንበኛው ይህን መመሪያ ተላልፎ ለሚወሰድበት ማንኛውም እርምጃ የሚያቀርበውን አቤቱታ ደንበኛው በሚገኝበት የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ታይቶ ውሳኔ ያገኛል፡፡ በውሳኔው ያልረካ ደንበኛ በተዋረድ ለባለስልጣኑ ም/ሥ/አስኪያጅ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጅ ማቅረብ ይችላል፣

10.9. የኢንዱስሪ ፍሳሽ ባለሰልጣኑ በሚያስቀምጠው የፍሳሽ ደረጃ በላይ የሆኑ ከሕዝብ የፍሳሽ መስመር ጋር እንዳይገናኝ ያደጋል፣ ክትትል ተደርጎ የተገኘ ደንበኛ የውሃ መስመሩ እንዲቐረጥ ተደርጎ በተቀመጠው ታሪፍ መሰረት 10 እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 11

## የጀት ማሰተር እና ሳንክሽን ትራክ አጠቃቀም

11.1. ባለስልጣኑ የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ ተሽከርካሪዎችን በራሱ ወጪ በመግዛት ያሰማራል፤

11.2. የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ ተሽከርካሪዎች የማደርያ ቦታ በተፈቀደለት ቦታ ብቻ ይሆናል፤

11.3. ቅርንጫፎች የጀት ማስተር /ሳንክሽን ትራክ አገልግሎት ሲፈልጉ በኘሮግራም ከቀጠሮ ጋር በማጣጣም ይመድብላቸዋል፤

11.4. የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ ኦፕሬተር ለመንግስት ሥራ፤ በግል ጉዳይ ወይም በአመት ፈቃድ ከስራ ቦታው ቢለይ የተሰጠውን የጀት ማስተር ለስምሪት የማስረከብ ግዴታ አለበት፤

11.5.እያንዳንዱ የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ  የተመደበበትን ተሽከርካሪ ንፅህናውን በመጠበቅ በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም  የጀት ማስተር ስምሪት በየሳምንቱ የፅዳትና የአካል ጉድሉት ፍተሻ በማድረግ ለዚሁ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት የፍሳሽ ንዑስ የሥራ ሂደት ወይም ለሚመለከተው ሪፖርት እንዲቀርብ ማደረግ አለበት፡፡

11.6.የጀት ማሰተር /ሳንክሽን ትራክ  አገልግሎት  ለጊዜው በማዕከል ይተዳደራል፤ በሂደት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊሟላ ይችላል፡፡

11.7.የጀት ማስተር/ሳክሽን ትራክ በጎርፍ ወይም በድንገተኛ አደጋ ወቅት በባለስልጣኑ፤ በዘርፍ ወይም በቅርንጫፍ ሥ/አስኪያጅ ትዕዛዝ ሊሰማራ ይችላል፣

## አንቀጽ 12

## የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ  አገልግሎት አሰጣጥ

12.1.የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ አገልግሎት ለደንበኞች የሚሰጠው በክፍያ ነው፤

12.2.ለደንበኞች አገልግሎት የሚሰጡ የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ በተመደበለበት ሰዓት ብቻ ይሆናል፡፡

12.3.ባለስልጣኑ የተዘጉ  የፍሳሽ መሰመሮችን ለመክፈት ከፍሳሽ ደህንንት ቁጥጥር ጋር በሚወጣ የጊዜ ሰሌዳ እና ጥገና ተግባር ይሰራል፤

12.4.ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚቀርበው ጥያቄ መሰረት ለመለስተኛ የፍሳሽ መስመር ፍተሻ ስራ ላይ ይውላል፤

12.5.የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ ስራ ላይ ለዋለበት ጊዜ ከአሰሪው ክፍል የውሎ ሪፖርት ይዞ የመምጣት ግዴታ አለበት፤

12.6.የጀት ማስተር/ ሳንክንሽን ትራክ ሲሰማራ በሥራ ትዕዛዝ ብቻ መሆን አለበት፣

12.7.አገልግሎት ያገኘ ደንበኛ አገልግሎቱን ያገኘበትን ሰአት እና አስተያቱን እንዲያሰፍር ይደረጋል ፡፡

## አንቀጽ 13

## የጀት ማሰተር / ሳንክሽን ትራክ ስምሪት

13.1. ማንኛውም የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ  ኦፐሬተር ይዞ ለሥራ ሲወጣ ተገቢው የተሽከርካሪ የስምሪት ቅጽ ከሚሰራው የፍሳሽ መስመር መጠን ጋር ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ብዛት ተገልፆ እንዲሰጠው መደረግ አለበት፡፡

13.2. እያንዳንዱ የጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ የግል ማህደር ተከፍቶለት የአገልግሎት እንቅስቃሴው በሃርድና ሶፍት ኮፒ ይደራጃል፤

13.3. ለስምሪት አሰጣጥ ያመች ዘንድ ጀት ማስተር / ሳንክሽን ትራክ  ስምሪት የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር የዋናው መ/ቤት፤ የቅርንጫፎችን  እና የደንበኞችን ጥያቄ ቀደም ተከተልና ባሉት ተሽከርካሪዎች ብዛት በማመጣጠን ከአንድ ቀን በፊት የስምሪት ኘሮግራም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

13.4. ጀት ማስተር /ሳንክሽን ትራክ  ኦፕሬተር  ከተመደቡበት ደንበኛ በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት አገልግሎት ሰለመስጠታቸው ማረጋገጫ ለስምሪት ቡድን ማቅረብ አለበት፡፡

13.5. በስብሰባ እና በልዩ ልዩ ምክንያት ጀት ማስተር /ሳንክሽን ትራክ    ሥራ ካልተሰራ ያልተሰራበትን መረጃ አጠናክሮ ይይዛል፤ በሥራ አፈፃፀም ላይ የገጠመው ትንታኔ ያቀርባል፤

13.6. የጀት ማስተሩ / ሳንክሽን ትራክ  በስምሪት ቅጹ ላይ ከተሞላው ውጭ በመንቀሳቀስ ነዳጅ አለአግባብ አለማባካና ቸውን የመቆጣጠርና መከታተል የስምሪት  ሃላፊነት ይሆናል፤

13.7. በዚህ አንቀጽ ተ.ቀ.6 መሠረት የነዳጅ አጠቃቀሙን ከተሰራው ሥራ ጋር የማመዛዘን ሥራ ይሰራል ተገቢው እርምጃ ይወስዳል፣

13.8. የጀት ማስተር /ሳንክሽን ትራክ   ስምሪት እና አፈፃፀም ዝርዝር ሪፖርት ለዚሁ በተዘጋጀው ቅጽ ተሞልቶ ለንዑሥ የሥራ ሂደቱ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.9. የጀት ማስተር /ሳንክሽን ትራክ  ስምሪት ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮችን  ለንዑስ የስራ ሂደት ሪፖርት በማቅረብ መፍትሄ ያሰጣል፡፡

13.10. በየወሩ መጨረሻ ለአገልግሎት የተወሰደውን ነዳጅና የተሰጠውን ደንበኞች አገልግሎት፤ የዋናው መ/ቤት ከፍተሻ ፍሳሽ መስመር የመክፈት እና ለቅርንጫፍ የዋለበት ጊዜ  ከኦፕሬተር  ጋር በመሆን ያመሳክራል ልዩነት ካለው መተማመን ላይ ይደረሳል፤ ሪፖርቱንም ለንዑሥ የስራ ሂደቱ ሪፖረት ያደርጋል፤

## <u>አንቀጽ 14</u>

## <u>የተቋረጠን መስመር ስለመቀጠል</u>

14.1 በህገወጥ ቅጥያ ምክንያት ወይም የአገልግሎት ዋጋ ባለመከፈሉ ወይም የተከለከሉ ቁሶችን ወደ ፍሳሽ መስመር በመልቀቁ የተቋረጠውን  መስመር ደንበኛው የሚፈለግበትን ሂሳብና ህገወጥ ድርጊቱ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ከፍሎ መስመር እንዲቀጠልለት ካመለከተ ባለስልጣኑ በደንበኛው መሉ ወጭ መስመሩን ሊቀጥልለት ይችላል፡፡

14.2 በህገወጥ መንገድ የተቀጠሉ መስመር በባለስልጣኑ የዲዛይንና የጥራት ደረጃ መሠረት የተሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ባለበት ሁኔታ እንዲቀጥል ሊደረግ ይችላል፡፡ ሆኖም

ህገ ወጥ ቅጥያውን የፈፀመው ባለይዞታ በደንብ ተላላፊነቱ ክስ የሚመሰረትበት ሲሆን ለመ/ቤቱም ተገቢውን ለቅጥያ የሚያስፈልገውን ወጪ ይከፍላል፡፡

14.3 በህገወጥ መንገድ ተቀጥሎ የተቋረጠበት ደንበኛ አስመልክቶ በባለስልጣኑ ተጠንቶ ወጭውን ክፍሎ መስመር ተዘርግቶ ቅጥያውን ይፈፅማል፡፡

## አንቀጽ 15

## ወደ ፍሳሽ መስመር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ ቁሶች

የሚከተሉት ቁሶች የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያዎችን የሚጎዱና የሚያውኩ ስለሆኑ በፍሳሽ መስመር ውስጥ እንዳይገቡ የተከለከሉ ናቸው፡-

ሀ/ ፀጉርና ላባ፣ የሞቱ እንስሳት

ለ/ ቤንዝን፣ ናፍጣ፣ የሞተር ዘይት፣ ስብና ቅባት፣ ሌሎች ኬሚካሎች

ሐ/ ማዳበሪያ፣ ጆንያ፣ ላስቲክ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ አጥንት፣

መ/ ድንጋይ፤ ጠጠር፣ አሸዋ፤ ብረታብረት እና ማናቸውም ጠጣር ነገሮች

ሠ/ የዝናብ ወይም የጎርፍ ውሃ፣ የተከማቸ ውሃ፣ ወደ ፍሳሽ መስመር ማስገባት፣

ረ/ የከብት ፈረስ፣ ደም፣እና መሰል ነገሮች

ሸ/ የፋብሪካና የግንባታ ተረፈ ምርቶች

## አንቀጽ 16

## ተጠያቂነት

16.1. ማንኛውም ባለንብረት ወይም ደንበኛ ሕገወጥ የፍሳሽ መስመር ቅጥያ ከፈፀመ ባለስልጣኑ የባለንብረቱን ወይም የደንበኛውን የውሃ አቅርቦት አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ ለማቋረጥ ይችላል፡፡

16.2. በተጨማሪም የድርጊቱ ፈፃሚ አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ መሠረት ያለበት ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገወጥ ቅጥያውን መቆረጡ ላስከተለው ወጪ ኪሳራ ኃላፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 17

## ቅጣት

17.1. በዚህ መመሪያ ላይ ጥሰት የሚፈፅም ሰራተኛ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና በህብረት ስምምነቱ መሠረት የዲሲፕሊን ቅጣት እና አግባብነት ባላቸው የወንጀልና ፍትሐብሄር ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

17.2. በዚህ መመሪያ ላይ ጥሰት የሚፈፅም አመራር በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እና አግባብነት ባላቸው የወንጀልና ፍትሐ/ብሄር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

17.3. በዚህ መመሪያ ላይ ጥሰት የሚፈፅም ደንበኛ ውል ማቋረጡ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባላቸው የወንጀልና ፍትሐ ብሄር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

17.4. በዚህ መመሪያ ላይ ጥሰት የሚፈፅም የስራ ተቋራጭ ወይም ማህበር በግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 3/2002 መሰረት ከማንኛውም የመንግስት ጨረታ ከ6 ወር ላላነሰ እና ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከአቅራቢነት እንዲሰረዝ የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚቀርብበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባላቸው የወንጀልና ፍትሐ ብሄር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 18

## መመሪያ የሚሻሻልበት ሁኔታ

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 19

## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዋናው ሥራ አስኪያጅ ተፈርሞበት እና የመ/ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አቶ አወቀ ኃ/ማሪያም
የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን
ዋና ሥራ አስኪያጅ